

# የኢየሱስ እንደገና ሕያው መሆን

የአርማትያሱ ዮሴፍ በመበላ የሚታወቀው ሰው ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን አስከሬን ጠየቀ። ዮሴፍ ባለጠጋ ሰው ሲሆን የኢየሱስ ደቀመዝሙር ነበር። የኢየሱስን አስከሬን ከመስቀል ላይ አወረደው። በጨርቅ ከከፈነው በኋላ በአዲስ መቃብር ውስጥ አስከሬኑን አኖረው።

ጲላጦስ አገረ ገዢው በኢየሱስ መቃብር ዙሪያ ወታደሮችን አኖረ። ምክንያቱም ደቀመዛሙርቱ የኢየሱስን አስከሬን ሰርቀው ኢየሱስ ተንስቷል ብለው ያሰወራሉ ብለው የሚሰጉ ሰዎች ስለነበሩ ነው።

በማለዳ እሑድ አንዳንድ ሴቶች ወደ መቃብሩ ማልደው ሄዱ። የኢየሱስን አስከሬን ለመቀባት በማሰብ ሽቶ ይዘው መጥተው ነበር። በዚያን ማለዳም ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ። መልአክ መጥቶም መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ አንከባለለው።. ከዚያም ባንከባለለው ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀመጠበት።

መልአኩም ወደ መቃብሩ ስፍራ የመጡትን ሴቶች “አትፍሩ፣ ኢየሱስ በዚህ የለም፣ እንደተናገረው ከሞት ተነስቷል።” አላቸው።

ይህንንም ለሌሎች ደቀመዛሙርት እንዲነግሩ አዘዛቸው። እየሄዱ እያሉም ኢየሱስ በመንገድ ተገናኛቸው። እንዲህም አላቸው “ወንድሞቼ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ንገሯቸው። እዚያ ያገኙኛል።”

ሁለት ሰዎች ኤማሁስ ተብሎ ወደሚጠራ መንደር እየተጓዙ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር እየተጨዋወተ አብሯቸው ይሄድ ነበር። ከቆይታ በኋላም አብሯቸው ማዕድ ተቀመጠ። Instantly they recognized him. በማዕድ

አብረው ተቀምጠው ሳሉም ኢየሱስ ራሱን ገለጠላቸው። እነርሱም ለሌሎቹ አስራ አንድ ደቀመዛሙርት የሆነውን ነገር ሊነግሯቸው ሄዱ።

ምንኛ ደስተኞች ነበሩ! ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል!

የኢየሱስ ትንሳኤ ታሪክ በሁሉም ወንጌላት ይገኛል። አሁን ከላይ ያየነው ታሪክ የሚገኘው በሉቃስ ምዕራፍ 24 ነው።

http://gardenofpraise.com